
# ቶፕስ ኤንድ ቦቶምስ (Tops & Bottoms)




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

**ጭብጦች (Themes)፤** እንስሳት (Animals)፤ ታማኝነት(Honesty)፤ ችግር መፍታት (Problem Solving)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** በአንድ ወቅት ሰነፍ ድብ (Bear) እና ብልህ ሀሬ (Hare) ነበሩ። ሃሬ ሀብታም እና ሰነፍ የሆነውን ድብ በማታለል ግማሽ ሰብሉን እንዲተው በማድረግ የቤተሰቡን ችግር እንዴት እንደሚፈታ ያንብቡ።

**ደራሲ፤**
ጃኔት ስቴቨንስ
(Janet Stevens)

**ሰዓሊ (Illustrator)፤**
ጃኔት ስቴቨንስ
(Janet Stevens)

## የንባብ ጊዜ!



**በፊት፤** የታሪኩን ርዕስ ያንብቡ እና ሽፋኑን ይመልከቱ። ልጅዎን በታሪኩ ውስጥ ምን ይከሰታል ብለው እንደሚያስቡ ይጠይቁት።

**በንባብ ጊዜ፤** በሚያነቡበት ወቅት፤“ሃሬ (Hare) ድብን (Bear) የሚረዳው እንዴት ነው? ሃሬ (Hare) ድብን (Bear) እንዴት ነው ያታለለው?” በማለት ይጠይቁ።

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ፤**

- ሃሬ (Hare) ድብን (Bear) እየረድስ ነበር ብለህ ታስባለህ? ለምን ሆነ ለምን አልሆነም?
- ድብ (Bear) ምን ተማረ?
- ድብ (Bear) በሚቀጥለው ጊዜ ምን ያደርጋል በለው ያስባሉ? ለምን ይመስልሃል?

## ሆን ተብሎ የሚደረግ ንግግር (INTENTIONAL TALK)

**የቋንቋ ግንዛቤ (Language Awareness)** ማለት “እንደ መጽሃፍ ማውራት (talking like a book)”ማለት ነው። ልጆች ብዙ ጊዜ ጮክ ብለው ሲነበቡ ሲሰሙ የተነደፉ ቋንቋዎችን ያስታውሳሉ፣ የሚነገሩት ቃላት እና የሚነበቡበት ቃና እና ሪትም። ልጆች ብዙውን ጊዜ የሚወዷቸውን ሐረጎች ወይም ገጾችን በማስታወስ ይደግማሉ። ይህ ከማስታወስ እጅግ በጣም በላይ ነው፤ ልጆች ታሪኮችን ሲነበቡ እንዴት ወደውስጣቸው የሚያሰርጹበት መንገድ ነው።

ቶፕስ ኤንድ ቦቶምስ (Tops & Bottoms) ለታሪኩ ጠቃሚ የሆነ ተደጋጋሚ ሀረግ ይዟል (“አዝመራው ሲያድግ ድብ ተኝቷል”) ልጅዎ ይህን ሀረግ ከእርስዎ ጋር እንዲናገር ያበረታቱት ወይም ደግሞ ደጋግመው ደጋግመው ስታነቡ ራሳቸው ይናገሩ።

## ተዛማጅ ተግባራት

**ላዮች (Tops)፤ መካከሎች (Middles)፤ እና ታችኞች (Bottoms)**

በቤቱ ዙሪያ ፍራፍሬዎችን እና አትክልቶችን ይያዙ ወይም ፎቶዎችን በመጽሃፍቶች ወይም በመስመር ላይ ይመልከቱ። የእያንዳንዱን አትክልትና ፍራፍሬ ላይ፣ መሃል እና ታች ተወያዩ። ልጅዎን “የትኛውን የፍራፍሬ/የአትክልት ክፍል ነው የምትበላው? በመሬት ውስጥ የሚበቅለው እንዴት ይመስልሃል?” በማለት ይጠይቁ። ፍራፍሬና አትክልት የሚያድጉት ለምን እንደሆነ ተወያዩ።



## ተጨማሪ ሪሶርሶች (ADDITIONAL RESOURCES)



**በጃኔት ስቴቨንስ (JANET STEVENS) የተጻፉ ሌሎች መጻህፍት**

- ሊትል ጉድ ዎልፍ (Little Good Wolf (2022))
- ዋይልድ አባውት አስ (Wild about Us! (2015))
- ኤንድ ዘ ዲሽ ራን አዌይ ዊዝ ዘ ስፑን (And The Dish Ran Away With The Spoon (2001))

©2025 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood